ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ረቢዕ ሳኒ 14/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚኒስቴር ኑቨምበር 19/2021 ግ.አ.

# ቤተሰብ ርጋታና ፍቅር ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
{ هُوَالَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَاحِدَةٍ وَجَعَلَ مِنْهَا زَوْجَهَا لِيَسْكُنَ إِلَيْهَا }

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡

(እርሱ ያ ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁ ከእርሷም መቀናጆዋን ወደርሷ ይረካ ዘንድ ያደረገ ነው፡፡) ማለት ነው፡፡

ብቸኛ አጋር የሌለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ እንድሁም ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸው እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል፡

ቤተሰብ የአንድ ማህበረሰብ መሰረትና የግንባታው ዋልታ ነው፡፡ የአንድ ማህበረሰብ አንዲነትና መረጋጋት እውን ሊሆን የሚችለው የቤተሰብ ውህደትና መረጋጋት ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም የእስልምና እምነት ከአባላቱ መካከል ርጋታ፣ ፍቅርና እዝነት ይሰፍን

ዘንድ ለቤተሰብ ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ وَمِنْ آيَاتِهِ أَنْ خَلَقَ لَكُمْ مِنْ أَنْفُسِكُمْ أَزْوَاجًا لِتَسْكُنُوا إِلَيْهَا وَجَعَلَ بَيْنَكُمْ مَوَدَّةً وَرَحْمَةً إِنَّ فِي ذَلِكَ لَآيَاتٍ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ }.**

(ለእናንተም ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደእነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ሕዝቦች ተዓምራቶች አሉሉ፡፡)

ይህችን አንቀጽ ጠለቅ ብሎ የሚመራመር ሰው የቤተሰብ ግንባታ ከአላህ (ዐ.ወ.) ታምራቶች አንዱ መሆኑን እንደገለጸች ሊገነዘብ ይችላል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ትዳርን የርጋታና ሰላም ምንጭ አድርጎታል፡፡ ይህውም አንድ ሰው ሚስት በማግባቱ እንዲሁም አንዲት ሴት ባል በማግባቷ ርጋታና ሰላምን ያገኛሉና ነው፡፡

እንድሁም አላህ (ሱ.ወ.) ፍቀርና እዘነትን የቤተሰብ መዋቅር መሰረት አድርጓል፡፡ ፍቅር መልካም ውለታን የሚያስከትል ባሕርይ ነው፡፡ በመሆኑም ባልና ሚስት አንዱ ከሌላው የሚከሰተውን ቦዘኔነት ወይም የሚታየውን የጠባይ ልዩነት በትግስት ያሳልፋሉ፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንዲህ ይላሉ፡ ( አንድ ሙእሚን ሙእሚን የሆነችን ሴት አይጥላ፡፡ ከሷ አንድን ጠባይ ቢጠላም ሌላ ጠባዩዋን ሊወድላት ይችላልና)፡፡

ይህን ማለትም የቤተሰብ መዋቅር የመልካም ሥነ ምግባር ትርጉም፣ ደግ ውለታና እዝነት ናቸው ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከተዋሀደና ከተረጋጋ ቤተሰብ መልካም ወዳጅነት ይስፋፋል፡፡ ምስጉን ባሕርይ ይፈጠራል፡፡ ደግ ዘርም ማፍራት ይቻላል፡፡ በመላ ቤቱም ውስጥ ደስታ ይሰፍናል፡፡

በአንድ ቤተሰብ ርጋታና ፍቅር ይሰፍን ዘንድ አባላቱ በበርካታ ጉዳዮች መታነጽ ይኖርባቸዋል፡፡ ከነሱም መካከል፡

ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙት ማሳመርና ለመልካም መኗኗር መገዛት የመጀመሪያው ሲሆን አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَعَاشِرُوهُنَّ بِالْمَعْرُوفِ}

(በመልካምም ተኗኗሩዋቸው፡፡)

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ለሴቶች ደግን ነገር እንዲታደርጉ አደራ እላችኋለሁ)፡፡ እንዲሁም እንድህ ይላሉ፡ (ከሴቶቻችሁ እጅግ ደጊቱ ያች ባሏ በሚያት ጊዜ የምታስደስተው፣ ባዘዛት ጊዜ የምትታዘዘው፣ ከቤት በወጣ ጊዜ ራሷንና ንብረቱን በመጠበቅ የምታስከብረው ነች)፡፡

ሌላው የመልካም ቤተሰብ መስፈርት ደግሞ አባውራው ምግብ፣ መጠጥና ልብስን በማሟላት ግዴታውን መወጣቱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{ وَعَلَى الْمَوْلُودِ لَهُ رِزْقُهُنَّ وَكِسْوَتُهُنَّ بِالْمَعْرُوفِ }

(ለእርሱም በተወለደለት (አባት) ላይ ምግባቸውና ልብሳቸው በችሎታው ልክ አለበት፡፡) እንዲሁም እንድህ ይላል፡

{لِيُنفِقْ ذُو سَعَةٍ مِّن سَعَتِهِ}

(የችሎታ ባለቤት ከችሎታው ይቀልብ፡፡)

ነብያችን እንድህ ይላሉ፡ (ከምጽዋት እጀግ በላጩ ከትርፍ ገንዘብ የሆነው ነው፡፡ የላይኛዋ እጅ ከታችኛዋ እጅ ትበልጣለች፡፡ ምጽዋት ስትሰጡ ቀለብ መስፈር ግድ በሆነባችሁ ሰዎች ጀምሩ)፡፡ እንድሁም እንድህ ይላሉ፡ ( አንድ ሰው ወንጀል ውስጥ ለምግባት ቀለብ መስፈር ያለበትን ሰው ሙብት አለመጠበቁ በቂው ነው)፡፡

ሌላው የመልካም ቤተሰብ መስፈርት ደግሞ ባልና ሚስት ከመካከላቸው ያለውን ምስጢር መጠበቃቸው ነው፡፡ ባልና ሚስት አንዱ ለሌላው ሽፋንና ማረፊያ ነው፡፡ ምስጢር ማውጣት ሃይማኖትም ሆነ ቅን ሥነ ምግባር የማይደግፈው ተግባር ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ

ይላሉ፡ (በትንሳኤ ቀን ከአላህ ዘንድ በደረጃ እጅግ ተንኮለኛው ሰው ለሚስቱ ምስጢር የነገረና ሚስቱም ምስጢር ነግራው ምስጢር ያወጣ ሰው ነው)፡፡

ሌላው የመልካም ቤተሰብ መስፈርት ልጆችን በማሳደግ፣ በቅኑ መስመር እንዲጓዙ በማድረግ ባልና ሚስት በጋራ መስራታቸው ነው፡፡ ልጆችን በማሳደግ ዘርፍ ያለው የባልና ሚስት ሚና ምግብ፣ መጠጥና ሌሎች ቁሳዊ ነገሮችን በማሟላት ብቻ ሊወሰን አይገባም፡፡ ይልቁንም በማህበረሰቡ እድገትና ብልጽግና ተፈላጊውን ሚና ለመጫወት ብቃት እንዲኖራቸው በመንፈሳቸው መልካም እሴቶችና ሥነ ምግባር ማስረጽንም ማካተት ይኖርበታል፡፡ ልጆች በዚህ መልኩ ሲያድጉ ለወላጆቻቸው በዚህች ዓለምም ሆነ በመጭው ዓለም የዓይን ማረፊያ ይሆናሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ وَالَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا هَبْ لَنَا مِنْ أَزْوَاجِنَا وَذُرِّيَّاتِنَا قُرَّةَ أَعْيُنٍ وَاجْعَلْنَا لِلْمُتَّقِينَ إِمَامًا }**

(እነዚያም «ጌታችን ሆይ! ከሚስቶቻችንና ከዘሮቻችን ለዓይኖች መርጊያን ለእኛ ስጠን፡፡ አላህን ለሚፈሩትም መሪ አድርገን» የሚሉት ናቸው፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( የሰው ልጅ ሲሞት ከሦስት ነገሮች በስተቀር ስራው ይቋረጣል፡፡ ቀጣይነት ያለው ምጽዋት ወይም ሰዎች የሚገለገሉበት እውቀት ወይም ለሱ ጸሎት የሚያደርግለት ልጅ)፡፡ የቤተሰብ አባላት ለልጆች ትኩረት እንደሚሰጡ ሁሉ የወላጆችንም መብት ማስከበር ይኖርባቸዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَقَضَى رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوا إِلَّا إِيَّاهُ وَبِالْوَالِدَيْنِ إِحْسَانًا}**

(ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፡- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፡፡ በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፡፡)

የዚያን ጊዜ በመላው የቤተሰብ አባላት ዘንድ ደህንነት፣ መረጋጋትና ደስታ ይሰፍናል፡፡

ሌላው የመልካም ቤተሰብ መስፈርት፣ መላው የቤተሰቡ አባላት በእለት ተእለት ጉዳዮች የጋራ ምክክር ማድረጋቸው ነው፡፡ ይህ ተግባር ሁሉም የቤተሰብ አባላት አስፈላጊነትና ልዩ ሚና ያለቸው መሆኑን ይገነዘባሉ፡፡ ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በሑደይቢያ እርቅ ባለቤታቸውን ኡሙ ሰለማን (ከርሳቸው አላህ ወደድና) አማክረዋታል፡፡ አስተያየቷንም ተቀብለው ተግባራዊ አድርገውታል፡፡ ለባቤታቸው በማማከራቸውም ደግ ነገር ተፈጥሯል፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የባልና ሚስት ዘመዶች ይህን ቤተሰብ በመጠበቅና የተራጋነቱን በማስቀጠል ዘርፍ ታላቅ ሚና ያላቸው መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ እነሱ የፍቀር ገመድ እንዲጠነክር፣ መከባበር፣ ርጋታና ፍቅር እንዲሰፍን ከባልና ሚስት መካከል ያለው የግል ጉዳይ እንዲከበር በማድረግና ለነሱም ምክርን በመስጠትና ቅኑን መንገድ በመምራት የሚፈጠረውን አለመግባባት በመቅረፍ የቤተሰቡን ህልውና ይጠብቃሉ፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

وَقُلْ لِّعِبَادِي يَقُولُوا الَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِنَّ الشَّيْطَانَ يَنزَغُ بَيْنَهُمْ إِنَّ الشَّيْطَانَ كَانَ لِلإِنسَان عَدُوًّا مُّبِينًا }

(ለባሮቼም በላቸው:- ያችን እርሷ መልካም የኾነችውን (ቃል) ይናገሩ:: ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና:: ሰይጣን ለሰው ግልጽ ጠላት ነውና::) እንዲሁም እንዲህ ይላል፡

**{ وَإِنْ خِفْتُمْ شِقَاقَ بَيْنِهِمَا فَابْعَثُوا حَكَمًا مِّنْ أَهْلِهِ وَحَكَمًا مِّنْ أَهْلِهَا إِن يُرِيدَا إِصْلَاحًا يُوَفِّقِ اللَّهُ بَيْنَهُمَا إِنَّ اللَّهَ كَانَ عَلِيمًا خَبِيرًا }**

(እናንተ ዋቢዎች) የመካከላቸውንም ጭቅጭቅ ብታውቁ ከቤተሰቦቹ ሽማግሌን ከቤተሰቦችዋም ሽማግሌን ላኩ:: ማስታረቅን ቢሹ አላህ በመካከላቸው ያስማማል:: አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነውና::)

እኛ በአሁኑ ወቅት በመላ ማህበረሰቡ ፍቅር፣ መግባባትና መረጋጋት ይሰፍን ዘንድ በቤቶቻችን ርጋታና ፍቅርን ማስፈን እጅጉን ያስፈልገናል::

**ربنا هب لنا من أزواجنا وذريتنا قرة أعين واجعلنا للمتقين إمامًا**

**አሚን**